# የመንፈሳዊ መሪ

# ተግባርና ግብ

ከዓለም አቀፍ የተልዕኮ ትምህርት ተቋም ጋር በመተባበር በሪክ ሲ ሃዋርድ ተዘጋጅቶ በመንፈሳዊ አገልግሎት ሰጪ ኮሚቴ አማካኝነት ከእንግሊዝኛ ወደአማርኛ የተመለሰ ስለመንፈሳዊ እድገት መማሪያ መጽሐፍ

1991 - አዲስ አበባ

ያሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

ማውጫ ገጽ


መግቢያ ---------------------------------------------------------- 3-4

ክፍለ ትምህርት

1. የሚያምኑና የሚከተሉ----------------------------------- 5-27
2. መሪዎች ሰዎችን ያደንቃሉ------------------------------ 28-48
3. አድገው ሌሎችን ያሳድጋሉ------------------------------ 49-71
4. ያቅዳሉ ያደራጃሉ----------------------------------------- 72-90
5. መልእክት ያስተላልፋሉ ----------------------------------- 90-112
6. ችግሮችን መፍታትና ውሳኔዎች ማስተላለፍ -----------112-134
7. ኃላፊነት ይቀበላሉ-------------------------------------------135-151
8. ዓላማችን እግብ ማድረስ ----------------------------------153-172
9. ራሳቸውን ገፋፍተው ሌሎችን መገፋፋት ---------------175-197
10. የሙከራ ፈተና መልሶች ---------------------------------200-205

# መግቢያ

ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ትምህርት የሚቀስሙት የጥንቶችን አባቶች በምሳሌነት በመከተልና የተሰጡ መመሪያዎችን አጥብቆ በመያዝ ነው። በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ስለ መንፈሳዊ መሪነት ለማስተማር የተዘጋጁት ዘጠኝ ተከታታይ ትምህርቶች በእነዚህ ሁለት መንገዶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ለመሪነት የተጠሩትን የእግዚአብሔር ሰዎችን ምሳሌነት ለመከተል ከጠራቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸውን መመሪያዎች አስቀድሞ ማወቅና መረዳት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘብ ለዚህ አገልግሎት ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ የሚረዳ መሆን አለመሆኑን የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይሆንም። የመንፈሳዊ መሪነትን አገልግሎት ለማዳበር ቅድመ ዝግጅት ወሳኝ ከመሆኑም በላይ ይህን አገልግሎት ለማዳበርና ተገቢ ያልሆኑ ስህተቶችን ለመቅጨት ይረዳል።

እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለውን እቅድና ዓላማ ሊፈጽም የሚችልበት መንገድ የእርሱን ዓላማና እቅድ ተከትለው ሌሎችም እንዲከተሉ ምሳሌ የሚሆኑና የሚመሩ ሰዎችን በመጥራትና በማስነሣት እንደሆነ ከብሉይም ሆነ ከአዲስ ኪዳን ለመረዳት እንችላለን። በዚህ መሠረታዊ እውነት ላይ በመመርኮዝ የአንድ መንፈሳዊ መሪ ዓላማና ማከናወን ያለበት ተግባር ማወቅና እንደዚሁም ለዚህ አገልግሎት መጠራቱን ማረጋገጡ ኃላፊነቱን በትክክል በመወጣት ውጤታማ ለመሆን እንዲችል ያግዘዋል። ለመንፈሳዊ መሪ ወሳኝ የሆኑ ሦስት ነገሮች ከስዎች ጋር መሥራት መቻልና ተግባርን በሚገባ መወጣት እንደዚሁም ለዚህ አገልግሎት መጠራትን ማረጋገጥ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ነው። እነዚህንም መረዳት፣ ብቃት፣ ጥሪ በማለት በሦስት ቃላት ልናጠቃልላቸው እንችላለን።

**መንፈሳዊ መሪነት** የተሰኘው የመማሪያ መጽሐፍ ስለ አመራር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ ተከታታይ ትምህርቶችን የሚያቀርብ ሲሆን፣ በአገልግሎት ሰፋ ያለ ልምድ ላላቸውም ሆነ ለጀማሪዎች እንደዚሁም ክርስቲያናዊ የአመራር ሥልጠና ለማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ እንዲጠቅም ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ዋና ትኩረቱም የመሪነት ስጦታዎችንና ብቃትን ማዳበር እንዴት እንደሚቻል አስፈላጊውን ገለጻ በመስጠት፣

በመሪዎችና በተከታዮች መካከል ሊኖር ስለሚገባው ትክክለኛ ግንኙነትና ትክክለኛ ትስስር ማድረግ ላይ ነው።

### የመጽሐፉ ዓላማዎች

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ተከታታይ ትምህርቶች ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

1. የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የአመራርን ሃሳብ ምሳሌ በመስጠት መግለጽ።
2. በመንፈሳዊ አመራር ውስጥ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን ተግባርና ዓላማ መግለጽ።
3. በራስህ ሕይወትና በሌሎች ውስጥ ያሉትን የመሪነት ስጦታዎችና ችሎታ ለይቶ በማወቅ ማመዛዘን።
4. የተለየ የመሪነት ችሎታን፣ ብቃትንና ዝንባሌን በማሳየት እነዚህ በሌሎችም ሕይወት እንዲዳብሩ መርዳት።
5. ክርስቲያናዊ ዓላማዎችን ተፈጻሚ በማድረጉ ረገድ ከሌሎች መሪዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ የራስህን ድርሻና ኃላፊነት መቀበል።

### የመጽሐፉ አጠቃቀም

መንፈሳዊ መሪነት የተባለው የመማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው በግልም ሆነ በጋራ ሆነው ምእመናን ትምህርቱን መከታተል ይችሉ ዘንድ እንደ አስተማሪ ሆኖ እንዲያገለግል የቀረበ ነው። አንድ ተማሪ በሚገባ ለመማር አስተማሪው የሚሰጠውን መመሪያ በጥንቃቄ መከተል እንደሚገባው ፣ ይህም መጽሐፍ የሚሰጠውን መመሪያ በጥንቃቄ መከተል አስፈላጊ ነው።

በእያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍሎች ማንበብ፣ የቀረቡትን ጥያቄዎች መመለስ፣ በየክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ የሚቀርቡትን የሙከራ ፈተናዎች በሚገባ ማጠናቀቅ ከእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሚጠበቅ ግዴታ ነው። ተከታታይ ትምህርቶቹን በሚገባ ለመከታተል የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መኖር አስፈላጊ ነው። ለዚህም የጥንቱና ቀለል ባለ አማርኛ የወጣው እትም ቢኖር ለማገናዘብ የሚረዳ ይሆናል።